ምሥጢረ ትንሣኤ

ትንሣኤ የሚለው ቃል ተንሥአ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ቃል ሲሆን መነሣት ማለት ነው። ነፍስና ሥጋ በሞት ከተለያዩ በኋላ በመጨረሻው ዘመን በትንሣኤ ይገናኛሉ። ስለ ትንሣኤ ስንናገር ልብ ልንለው የሚገባ ቁም ነገር ቢኖር ስለ ሥጋ ትንሣኤ መናገራችን መሆኑን ነው። ምክንያቱም ነፍስ በባሕርይዋ የማትሞት የማትፈርስና የማትበሰብስ ናት። ስለዚህ ትንሣኤ የሚሆነው ሥጋ ሞቶ ፈርሶና በስብሶ ይኖር ከነበረበት ከመቃብር በሥልጣነ እግዚአብሔር ተነሥቶ ከነፍስ ጋር በመዋሐድ ነው። ምሥጢረ ትንሣኤ በብሉይና በሐዲስ የተገለጠ እውነታ ነው።

ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን

ምንም እንኳ ምሥጢረ ትንሣኤ እንደ ዘመነ ሐዲስ በብሉይ ኪዳን በግልጽና በተብራራ መንገድ የተገለጸ ባይሆንም በትንቢትና በምሳሌ ሸሽግና ስውር ሆኖ ተገልጦ እንደነበር መረዳት አያደግትም። በብሉይ ኪዳን ለምሥጢረ ትንሣኤ መነሻ የሚሆኑ ጥቅሶች ለአብነት ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. አባታችን አብርሃም የሚወዳት ሚስቱ ሣራ በሞት በተለየችው ጊዜ *"እኔ በአናንተ ዘንድ ሰደተኛና መጻተኛ ነኝ" ዘፍ 23÷4* በማለት ተናግሮ ነበር። ይህ አነጋገሩ አብርሃም በሙታን ትንሣኤ ላይ ተስፋ እንዳለው የሚያመለክት ነበር። እንዴት ቢሉ ምላሹን ከሐዋርያው ቃል እንረዳለንና ነው። *"እነዚህ ሁሉ ለምነው ሞቱ፣ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና። ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፣ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ። እንግዲህ የሚሉት ለአነርሱ የሚሆነውን አገር እንዲፈልጉ ያመላክታሉና። ያን የወጡበትን አገር አሰበው ቢሆኑ፣ ሊመለሱም ጊዜ በሆነላቸው ነበር። አሁን ግን የሚበልጠውን አርሱም ሰማያዊት አገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በአነርሱ አያፍርም፣ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና"።- ዕብ 11÷13-16*

Scanned by CamScanner

ከጥቅሱ እንደምንረዳው አብርሃምም ሆነ ሌሎቹ ቅዱሳን በዚህ ምድር የኖሩት እንደ እንግዳና መጻተኛ እንደ ነበርና እነርሱ ግን በትንሣኤ ላይ ተስፋ ስለነበራቸው "ለማያዊውን አገር ይናፍቃሉ" ተባለ::

ከዚህም ሌላ አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ለመሠዋት ሲዘጋጅ እግዚአብሔር ከሞት ሊያስነሣለት እንደሚችል በማመን ነበር:: ይህም የትንሣኤ ምሳሌ ነው:: "በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል የተባለለት አርሱ አንድ ልጁን አቀረበ አግዚአብሔር ከሙታን ሊያነሣው አንዲቻለው አሰበአልና፣ ከዚህም ደግሞ በምሳሌ አገኘው" ዕብ ፲፩÷19 እንዲል::

2. የትዕግስት አባት ኢዮብም በተስፋ ትንሣኤ ላይ ያለውን እምነት የሚያስገነዝብ ንግግር ተናግሮ ይገኛል "በውኑ ሰው ከሞተ በኋላ ተመልሶ ሕያው ይሆናልን" ኢዮ 14÷14 ሲል ጠይቋል:: በተጨማሪም "ዛፍ ቢቆረጥ ደግሞ ያቆጠቁጥ ዘንድ፣ ቅርንጫፉም አንዳያልቅ ተስፋ አለው:: ሥሩም በምድር ውስጥ ቢያረጅ፣ ግንዱ ቅርንጫፍ ያወጣል" ኢዮ 14÷7-9 በማለት በትንሣኤ ላይ ያለውን ተስፋና እምነት ከዛፍ መቆረጥና ተመልሶ ማብቀል ጋር አዛምዶ ተናግሯል::

3. ዳግመኛም በሙታን መነሣት ላይ ያለውን ተስፋ በሚያመለክት አነጋገር "እኔ ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ፣ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፣ ይህ ቁርቤቴ ከጠፋ በኋላ፣ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ አግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ፣ እኔ ራሴ አየዋለሁ፣ ዓይኖቼም ይመለከቱታል ከእኔም ሌላ አይደለም:: ልቤ በመናፈቅ ዝሏል" ኢዮ 19÷ 25-27 በማለት በትንሣኤ ጌታን ማየት እንደሚናፍቅ ተናገረ::

4. ነቢዩ ዳዊትም ስለ ትንሣኤ ሲናገር "ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፣ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም" መዝ 16÷9-10 በማለት ለጊዜው ስለ ራሱ ፍጻሜው ግን ስለ ጌታችን ትንሣኤ ተናገረ::- የሐ 2÷24-32

Scanned by CamScanner

5. ነቢዩ ሕዝቅኤል ትንሣኤን በተመለከተ *"ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል:: እነሆ-ትንፋሽን አገባባችኋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ"* ሕዝ *37÷5* በማለት ተናግሯል::
6. ነቢዩ ዳንኤልም ስለ ትንሣኤ *"በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ አኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት ፣ አኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና"* ዳን *12÷2-3* ብሎ ትንቢት ተናገረ::
7. ነቢዩ ኢሳይያስ *"ሙታን ሕያዋን ይሆናሉ ሬሣዎችም ይነሣሉ በምድርም የምትኖር ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለች ንቁ ዘምሩ"* ኢሳ *26÷19* በማለት ስለ ትንሣኤ ትንቢት ተናገረ::
8. ነቢዩ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እድሮ መውጣቱ ጌታችን ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር የማደሩ ምሳሌ ነው:: ይህንም ጌታ ራሱ አረጋግጦልናል::- *ማቴ 12÷40 ትጽና 2÷1፣ ዮናስ 3÷5*

የጌታችን ትንሣኤ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የከበረና የደስታ ሁሉ ምንጭ ነው:: በትንሣኤው የዲያብሎስ ኃይል የተሻረበት መቃብር የተዋጠበትና ሞት ራሱ የሞተበት ስለሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ የጌታ ትንሣኤ በታላቅ ክብርና ደስታ የሚታሰብ ነው::

ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው እንደሚሞትና በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ደጋግሞ ተናግሮ ነበር *ማቴ 20÷19፣ ሉቃ 18÷31-33፣ ማቴ 27÷ 62 64* በኋላም የተናገረውን ቃል በተግባር በመፈጸም ሞትን ድል አድርጐ በመነሣት ትንሣኤውን አማናዊ አድርጓል::- ዮሐ 20

ጌታችን ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት ቅድስት ነፍሱን ከከቡር ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለየ ዮሐ 19÷30:: አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ሥጋውን ከመቃብር አውርደው በአይሁዱ የአገናነዝ ልማድ ሸቱ ቀብተው በተልባ እግር ልብስ ከፍነው

Scanned by CamScanner

ማንም ባልተቀበረበት የአርማትያሱ ዮሴፍ ለራሱ ባዘጋጀው አዲስ መቃብር ቀበሩት። የመቃብሩም ደጃፍ በታላቅ ድንጋይ ተዘጋ በማኅተምም አተሙት- *ማቴ 26÷57-61* ።

ጌታችን ቅድስት ነፍሱን ከከቡር ሥጋው በለየ ጊዜ በሥጋው ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በመቃብር አደረ። በነፍሱ ደግሞ ወደ ሲኦል ወርዶ በዚያ ለነበሩ ነፍሳት ነጻነትን ሰበከላቸው ነጻም አወጣቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ እንደተናገረ *"በሥጋ ሞቶ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፣ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው"* ።- *፩ጴጥ 3÷13- 19*

በዚህ ጊዜ ከተዋሕዶ በኋላ መለኮትና ትስብእት ለቅጽበተ ዓይን እንኳ መለያየት የለባቸውምና መለኮት ከሥጋ ጋር ወደ መቃብር በመውረዱ ሥጋን ሞቶ ፈርሶና በስብሶ እንዳይቀር አደረገው። ከነፍስ ጋር ደግሞ ወደ ሲኦል በመውረድ ነፍሳትን ከዲያብሎስ ማርኮ ነጻ አወጣ።

የካህናት አለቆችና ጸሐፍት ፈሪሳውያን ጌታችን ከተቀበረ በኋላ በሕይወት ሳለ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ እንዳለ ትዝ አላቸው። በዚህ ጊዜ ከጲላጦስ ፈቃድ ጠይቀው መቃብሩን አተሙ በጭፍሮችም አስጠበቁ። በዚህም የትንሣኤው አማናዊነት ተረጋገጠ።

-*ማቴ 27÷62-66*

ከርስቶስ ጌታችን እንደተናገረ በሦስተኛው ቀን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ከፈቱልኝ ሳይል ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሞት ተነሣ። በዚህም የነቢያት ትንቢት ተፈጸመ *መዝ ÷ 85 መዝ ፲፩÷5 መዝ 3÷5 መዝ 106÷16*። ከተነሣም በኋላ መጀመሪያ ለመግደላዊት ማርያም ቀጥሎ ለሌላይቱ ማርያም *(ለማርያም ባውፍልያ)* ቀጥሎ ለጴጥሮስ በመቀጠል ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት በኋላም ለኤማሁስ መንገደኞች በኋላም ለተወሰኑ ወንድሞችና ለጠርሴሱ ሳዖል ታየ። ትንሣኤውም በሁሉም ዘንድ ተረጋገጠ።

Scanned by CamScanner

ጌታችን ለምን ተነሣ?

ጌታችን ከሞት የተነሣበት አያሌ ምክንያቶች ቢኖሩም የተወሰኑትንና ዋናዎቹን ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ ለምን ተነሣ ቢሉ?

፡. በእርሱ ሕይወት ስለነበረች

መጽሐፍ እንደሚናገረው በእርሱ ሕይወት ስለነበረ ሞቶ ሊቀር አይችልም ፡፡ በሌላ አነጋገር እርሱ ሕይወት ነውና ሞቶ ሊቀር አይችልም *"ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ" ዮሐ ፲፩÷25* እንዳለ፡፡ ዳግመኛም *"እኔ መገድና እውነት ሕይወትም ነኝ"* ብሏል *ዮሐ ፲፬÷6* ጌታችን ሕይወት ስለሆነ መልአኩ ለመግደላዊት ማርያም *"ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ" ሉቃ 24÷5* በማለት *"ሕያው"* ብሎ ጠርቶ በባሕርይው ሕይወት በመሆኑ ሞቶ ሊቀር እንደማይችል መሰከረ፡፡-ዮሐ፡4

2. ለሙታን ሕይወት ሰጪ ስለሆነ

በኦሪት ነቢዩ ኤልያስና ነቢዩ ኤልሳዕ ከተደጋጋሚ ጸሎትና ልመና በኋላ ሙት አንሥተዋል፡፡ እርሱ ግን ጌታችን በቃሉ *(በትእዛዙ)* ብቻ የምኩራብ አለቃውን ልጅ ጣሊታን *ማር 5÷35-43*፤ ናይን በተባለች ከተማ የመበለቷን ልጅ *ሉቃ 7÷11-15* እና ወዳጁ አልዓዛርን ከሞት አንሥቷል *ዮሐ ፲፩÷43* ስለዚህ የሙታን አንሺ ነውና መነሣቱ የግድ ነበር፡፡ *"አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፣ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣል" ዮሐ 5÷21* ተብሎአል፡፡

3. ሞትን ለመደምሰስ

በመነሣቱ በሞት ላይ ያለውን ሥልጣን አውቀናል፡፡ ሞትም አስፈሪነቱ ቀርቶ *" ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ድል መንሣትህ ወዴት አለ?" ፩ቆሮ15÷55* ተብሎ እንዲላገድበት ሆነ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስና ቅዱስ አውግስጢን በጌታ ትንሣኤ *" ሞት"* እንደሞተ ለማመልከት ትንሣኤውን *" የሞት ሞት"* ብለውታል፡፡ ሞት ራሱ የሞተበት ነው ለማለት ነው፡፡

Scanned by CamScanner

4. መለኮታዊ ባሕርይው ከሥጋ ባሕርይው እንዳልተለየ ለማመልከት

ጌታ ሞተ ስንል የነፍሱ ከሥጋው መለየት ነው። መለኮት ግን አስቀድመን እንደገለጽነው ከሥጋም ከነፍስም ለቅጽበት አልተለየም። ይህ ባይሆን ኖሮ ሥጋ በራሱ እንዴት ሊነሣ ይችል ነበር? በመነሣቱ ግን መለኮት እንዳልተለየው አሳየ። ሐዋርያው ይህን ምሥጢር ሲናገር *"ወደ ምድር ታችኛው ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፣ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው÷ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው"* ኤፌ 4÷10 በማለት የወረደው (ሥጋ) እና ከሰማያት በላይ የወጣው (መለኮት) አንድ ናቸው አልተለያዩም ለማለት *"ያው ነው"* ብሎ ተናገረ።

5. በሥልጣኑ እንደሞተና እንደተነሣ ለማመልከት

ጌታችን ስለ ራሱ ሲናገር *"ነፍሴን...ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ"* ዮሐ 10÷18 በማለት እንደተናገረ መነሣቱ በፈቃዱና በሥልጣኑ እንደሆነ ያሳያል። በሌላ ስፍራ ***"ወተንሣእኩ አሰመ አግዚአብሔር አንሥአኒ"*** እግዚአብሔር አንሥቶኛልና ተነሣሁ መዝ 3÷5 [57] የሚል ቃል መኖሩ በሥልጣን በኃይል በፈቃድ አንድ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ነገር ግን ሞቱና ትንሣኤው በፈቃዱ ስለሆነ *"እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ እርሱ እስኪፈልግ ድረስ ፍቅርን እንዳታሥነሡትና እንዳታነሣሡት በሚዳቋ በምድረ በዳም ዋላ አምላችኋለሁ"* መኃ 2÷7 ተባለ።

57. በሌላ ስፍራ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ከሙታን እንዳስነሣው ተገልጿል ሮሜ 8÷11 በዚህም መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በሥልጣንና በፈቃድ አንድ መሆኑ ይመሰከራል።

Scanned by CamScanner

6. **ትንቢቱን ለመፈጸም**

ጌታችን በሕይወት ሳለ ገና በተደጋጋሚ ተላልፎ እንደሚሰጥና እንደሚሞት በሦስተኛውም ቀን እንደሚነሣ ተናግሮ ነበር *ማቴ 16÷21፣ ማቴ 17÷9፣ ሉቃ 9÷31-33* በመሆኑም ከተነሣ በኋላ ሰዎች እነሣለሁ ማለቱን ማስታወስ ጀመሩ። መልአኩም ለሴቶች ሲናገር *"እንደ ተናገረ ተነሥቷል" ማቴ 28÷5-6* ነበር ያላቸው። እንደ ተናገረ ማለት እንደተነበየው ከማለት ጋር አንድ ነው። በተጨማሪም በነቢያት ስለ መነሣቱ ተነግሮ ነበር።- ሉቃ 24÷44-46

7. **ደቀ-መዛሙርቱን ለማጽናናትና ለማበረታት**

በጌታ ሞት ምክንያት ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የተበተኑ የተደበቁና የካዱ ነበሩ። በመነሣቱ ግን የተበተኑ ተሰበሰቡ የተደበቁ ተገለጡ የካዱ ተመለሱ ለኀዘናቸው መጽናናት ለፍርሃታቸው ብርታት አገኙ።

8. **እንደማንኛውም ሰው እንዳልሆነ ለማሰረዳት**

ሰዎች ሁሉ እስከ ትንሣኤ ዘጉባኤ ሞተው መቆየት ግዴታቸው ነው እርሱ ግን ከሌሎች በተለየ ሰው የሆነ አምላክ ስለሆነ ፈጥኖ በገዛ ፈቃዱ ተነሣ። በዚህም ከሌሎች የተለየ መሆኑን አሳየ።

9. **ላንቀላፉት የትንሣኤያቸው በኩር ለመሆን**

ክርስቶስ ከሞት በመነሣቱ በእርሱ አምነው ያንቀላፉት ሁሉ ለከብር ትንሣኤ የሚነሡበት ኃይል ከእርሱ ስለሚያገኙ ለትንሣኤያችን በኩር ይሆን ዘንድ ተነሣ ።- ፩ቆሮ 15÷20-22

10. **ክርስትናን ለመመሥረት ተነሣ**

ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በቆየባቸው አርባ ቀናት ስለ መንግሥቱ ነገራቸው የሐ፩÷3። በተጨማሪም የእምነት መመሪያዎችንና ክህነትን ሰጣቸው ዮሐ 20÷22-23 ቀጥሎም በስመ ሥላሴ እያጠመቁ ሰዎችን እያስተማሩ

Scanned by CamScanner

በዓለም ሁሉ እንዲዞሩ በማዘዝ *ማቴ 28÷19* ከርስትና መሠረቱን እንዲጥል አደረገ::

የትንሣኤው አማናዊነት

የጌታችን የኢየሱስ ከርስቶስ ከሞት መነሣት ለከርስትና ሃይማኖት የማዕዘን ደንጊያ ነው:: ትንሣኤው ዓለምን የለወጠ ምሥጢር ነው:: ትንሣኤው ኃይል ነው:: ጌታ ከሞት ባይነሣ ኖሮ ከርስትና አይኖርም ነበር:: በመሆኑም የጌታ ትንሣኤ የከርስትና ሃይማኖት መሠረት ነው ማለት ምክንያታዊ አባባል ነው::የጌታ ትንሣኤ ፍጹም ድኅነታችንን ያሳያል::ምክንያቱም አስቀድሞ እንደሚነሣ ተናግሮ ስለነበር የተናገረው ሁሉ እውነት መሆኑን አረጋገጥን::

በትንሣኤው አማናዊነት (እውነተኝነት) ማመን በእምነት ውስጥ ወሳኝ ነገር ነው:: በጥንት ዘመን የነበሩ ከርስቲያኖች ሲገናኙ *"ከርስቶስ ከሙታን ተነሣ...በእውነት ተነሣ"* በማለት ሰላምታ ይለዋወጡ ነበር::ወይም ደግሞ *"ማራናታ"* በሚል ቃል ሰላምታ ይሰጣጡ ነበር:: ትርጉሙ *"ከርስቶስ የተነሣው ያረገውና ዳግም የሚመጣው"* ማለት ነው:: እነዚህ የከርስቶስን ትንሣኤ አማናዊነት የሚያመለክቱ ሰላምታዎች ከርስቲያኖች በከርስቶስ ትንሣኤ አማናዊነት ላይ ያላቸውን ጽኑ እምነት የሚያሳዩ ናቸው::

የከርስቶስ ትንሣኤ አማናዊ ባይሆን ኖሮ ከርስትና ምን ያህል ከንቱነት ይሆን እንደነበር ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ *"ከርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን እንዴት የለም ይላሉ? ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ከርስቶስ አልተነሣማ፤ ከርስቶስ ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት.... በዚህች ሕይወት (በምድራዊ ሕይወት) ብቻ ከርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፣ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን"* በማለት ያለ ከርስቶስ ትንሣኤ በከርስትና ያለው ሁሉ ከንቱ እንደሚሆን ገለጸ- *1ቆሮ 15÷12-19::*

Scanned by CamScanner

ምንም እንኳ የክርስቶስ ከሞት መነሣት በብዙ መንገዶች የተረጋገጠ ቢሆንም አይሁድ እና አንዳንድ ወገኖች ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ያደረጋቸውን ተአምራቶች እንዳሳበሉ ሁሉ ትንሣኤውንም ሊያስተባብሉ ሞከረው ነበር::

የአይሁድ ክህደት በትንሣኤው ላይ

የጌታችን ከሞት መነሣት በጊዜው በነበሩ አይሁድ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤ የፈጠረ ክስተት ነበር::ስለሆነም በተለመደው ክህደት በመጽናት ትንሣኤውን ካዱ:: ትንሣኤውን ለማስተባበልም ቆርጠው ተነሡ::

አይሁድ ጌታችን ከመነሣቱ በፊት በመዋዕለ ሥጋዌውም ሆነ ከሞት ከተነሣ በኋላ ትንሣኤውን ለማሳበል ሞክረዋል:: ጌታ ከትንሣኤው በፊት በተደጋጋሚ ተላላፎ እንደሚሰጥ መከራ እንደሚቀበልና እንደሚሞት በሦስተኛውም ቀን ከሞት እንደሚነሣ በዝርዝርና በግልጽ ተናግሮ ነበር *ማቴ 20÷18-19፣ ማር10÷33-34፣ ሉቃ18÷31-33::*

ስለዚህ አይሁድ ጌታ *"በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ"* ማለቱ ትዝ ብሏቸው የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ ቀርበው " ጌታ ሆይ ያ አሳች በሕይወቱ ገና ሳለ ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ እንዳለ ትዝ አለን:: እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁ ለሕዝቡም ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ፣ የኋለኛይቱ ስሕተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩን እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት:: ጲላጦስም ጠባቆች አሉላችሁ ሄዳችሁ እንዳወቃችሁ አስጠብቁ አላቸው:: እነርሱም ሄደው ከጠባቆቹ ጋር ድንጋይን አትመው መቃብሩን አስጠበቁ"::- *ማቴ 27÷62-66*

መቃብሩ በድንጋይ መዘጋቱ፣ መታተሙና ጠባቂዎች እንዲጠብቁ መደረጉ ወይም አይሁድ የወሰዱት ይህ ሁሉ ጥንቃቄ በተቃራኒው የትንሣኤውን አማናዊነት የሚያመለክት ነበር:: ምክንያቱም በዚህ ሁሉ ጥንቃቄቸው ካልተነሣ ታዲያ ምን ሆነ ይባላል? አይሁድ ጌታን በአንድ ወቅት በሰንበት ዓይነ ስውሩን በማብራቱ ሰንበትን

Scanned by CamScanner

በመሻር ከሰሰውት ነበር:: እነርሱ ግን በሰንበት የመቃብሩን ዓለት አንከባለው ሲዘጉ አላፈሩም::- *ዮሐ 9÷16-24*

የተልባ እግርና ጥምጣም

ለጌታ ትንሣኤ ማረጋገጫ ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ ጌታ የተገነዘበት የተልባ እግርና ጥምጣም አንዱ ነው:: *"ጴጥሮስም... ወደ መቃብሩ ገባ፣ የተልባ አግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፣ ደግሞ በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው በአንድ ሥፍራ እንደነበረ እንጂ ከተልባ አግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበር አየ"* ዮሐ *20÷6-7* ይላል:: ይህ አገላለጽ ያለ ምክንያት የተቀመጠ አይደለም:: ምክንያቱም የተልባ እግር ልብሱና በራሱ ላይ የነበረው ጥምጣም ተለያይተው መቀመጣቸው ለጌታ ትንሣኤ አማናዊነት ዓይነተኛ ማረጋገጫ ስለሆነ ነው::

በኢይሁድ አባባል ሄደን የጌታ ሥጋ ተሰርቆ ከሆነ ሰራቂው እንዴት ከፈኑን ከሰውነቱ ማለያየት ቻለ? የዚህስ ነገር ዓላማው ምንድነው? ሰራቂ ከአሁን አሁን መጡብኝ እያለ ይቸኩላል ወይስ ጊዜ አግኝቶና ተረጋግቶ ከፈኑን ለብቻ ጥምጣምን ደግሞ ለብቻ ያስቀምጣል? ጠባቆቹስ በጥበቃ ላይ ሳሉ እንዴት ይህ ሁሉ ተቻለ? ስለዚህ ይህ ሊሆን የማይችል ስለሆነ የከፈኑና የጥምጣሙ ለብቻ መቀመጥ ጌታ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል የመነሣቱ ማረጋገጫ ነው::

በዮሐንስ ወንጌል 20 ቁጥር 9 ላይ *"በዚያን ጊዜ አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣው ሌላው ደቀ መዝሙር (ዮሐንስ ነው) ደግሞ ገባ አየም፣ አመነም"* ተብሎ መነገሩ ዮሐንስ የተመለከተው ጌታ ሲነሣ አይደለም:: ነገር ግን ከፈኑንና ጥምጣሙን አይቷል:: ይህ ደግሞ ለትንሣኤው አስረጅ ስለሆነ *"አየም አመነም"* ተባለ::

ደቀ መዛሙርቱ በድኑን ሰርቀዋልን?

የአይሁድ ትንሣኤውን የማስተባበል ተቃውሞ ቀጥሏል:: ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተው እኛ ተኝተን ሳለ በሌሊት ደቀመዛሙርቱ ሰረቁት በሉ እኛም ለገዢው

Scanned by CamScanner

እናስረዳዋለን ተባባሉ:: ጭፍሮችም ገንዘብ ተቀብለው እንደ ታዘዙት አደረጉ ማቴ 28÷11-15 ይላል::ይህስ ሊሆን የሚችል ነገር ነው?

እንዲህ ብሎ ማመን ሊመለሱ ከማይችሉ ጥያቄዎች ጋር መጋፈጥ መሆኑን አይሁድ ልብ ያሉት አይመስልም:: ትንሣኤውን ለማስተባበል ያደረጉት ማንኛውም ጥረት የትንሣኤውን አማናዊነት ከማስረዳቱ ባሻገር የሞተውና መከራ የተቀበለውም በገዛ ፈቃዱ ለመሆኑ ምስክር ነው:: እንዴት ቢሉ ሁሉንም በዝርዝር ተናግሮት ነበርና ነው:: እኛ ግን ደቀ-መዛሙርቱ በድኑን አልሰረቁም የምንልበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው::

1. በመስረቃቸው ምን የሚጠቀሙት ነገር አለ? ይልቁንም እንኳን ሊሰርቁ አይሁድን ፈርተው እንደተበታተኑ ግልጽ ነው::
2. ካልተነሣ ስለምን ትንሣኤውን በመስበካቸው ለመከራና ለሞት ተላልፈው ይሰጣሉ፣ ሐሰት ከሆነና ደቀ መዛሙርቱም ሰርቀው ከሆነ ለጌታም ሆነ ለራሳቸው ክብር አይሰጡም ማለት አይደለም?
3. እንዴትስ ብለው ነው ጠባቆቹን አልፈው የሄዱት? እንዴትስ ነው ያለ ምንም ኮሽታ ድንጋዩን ያንከባለሉት? በድኑንስ እንዴት በሰንበት ተሸከሙ?
4. ወታደሮቹ እንቅልፍ ጣላቸው ቢባል እንኳ እንዴት አስጨናቂውን የሮማን ሕግ ቸል ብለው እንቅልፍ ወሰዳቸው? በፈረቃስ መጠበቃቸው እንዲህ ዓይነቱን ነገር ለመከላከል አይደለምን? ከጠባቆቹ አንዱ እንኳን እንዴት አልነቃም? በጥፋታቸውስ ለፍርድ ቀርበው ለምን አልተቀጡም? ጉዳዩስ ለምን በሹሞች አልተመረመረም?
5. በድኑንስ ሰርቀው የት ወሰዱት? በሰንበትስ ወደየትና እንዴት ቀበሩት? ጠባቆች ተኝተው ከነበረ በደቀ መዛሙርቱ መሰረቁን እንዴት አወቁ?
6. ትንሣኤውስ ሐሰት ከሆነ ሐሰተኛ በሆኑ ሐዋርያት እጅ ተአምራት ሊደረግ ይችላል?

Scanned by CamScanner

በነዚህ ሁሉ ማረጋገጫዎች የተነሣ የጌታ ትንሣኤ አማናዊ ነው እንላለን። ለዚህም ነው ሐዋርያት በስብከታቸው ደጋግመው "ኢየሱስ" እና "ትንሣኤ" የሚለውን ቃል ያነሡ የነበረው የሐ 17÷18 ማን ውሸት ለሆነ ነገር ለመከራና ለሞት ተላልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ይሆናል። እኛ ግን "ጌታ በእውነት ተነሥቶአል" ሉቃ 24÷34 እንላለን። ማራናታ!

ሰብአዊ ባሕርይው ከትንሣኤ በኋላም ተረጋግጧል

ጌታችን የተነሣው አስቀድሞ ለብሶት በነበረው ሥጋ ነው። "ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም" የሐ2÷27 ተብሎ እንደተነገረ ሥጋው በመቃብር ፈርሶና በስብሶ አልቀረም።

ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ሥጋዊ ባሕርይውን እንዳልተወ ለማጠየቅ "እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔም እንደምታዩት፣ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳሰሳችሁ እዩ አላቸው። ይህንንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው...በዚህ እንዳች የሚበላ አላችሁ አላቸው። እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ እንድ ቁራጭ፣ ከማር ወለላም ሰጡት ተቀብሎም በፊታቸው በላ" ሉቃ 24÷39-43 ተብሏል።

እዩኝ ማለቱና በፊታቸው መብላቱ ሰብአዊ ባሕርዩን ትቶ እንዳልተነሣ ለማመልከት ነው። በዚህ ዓይነት ራሱን መግለጡ ለደቀ መዛሙርቱ በእምነታቸው ጽኑአን እንዲሆኑ አስችሏቸዋል ፩ዮሐ1÷1።

ጌታችን ከሙታን ከተነሣ በኋላ እስከ ሚያርግበት አርባ ቀን ድረስ በተደጋጋሚ ለደቀ መዛሙርቱ ታይቷቸዋል። በመዓልትና በምሽት፣ በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ፣ በቤትና በጎዳና፣ በባሕር ዳርቻና በተራራ ተገልጦ ታይቷቸዋል። በዚህም በሥጋ ባሕርይው እንደተነሣ ከማጠየቁ ባሻገር ለእምነታቸው ጽናት በመሆን የቶማስን ጥርጥር የቅዱስ ጴጥሮስን ኀዘን የመግደላዊት ማርያምን የኀዘን ዕንባ አስወግዷል።

Scanned by CamScanner

በከበረ ሥጋ መነሣት ምንድነው?

የጌታ ትንሣኤ የተከናወነው በከበረ ሥጋ ነው። ይህ ማለት ምንም እንኳ ጌታ ከተነሣ በኋላ ሥጋዊ ባሕርይውን ባይተወውም ነገር ግን ከትንሣኤ በፊት አስቀድሞ ከነበሩ ሁኔታዎች የሚለይበት ነገር አለ።

ከትንሣኤው በፊት ከኃጢአት በቀር ሥጋ እንደኛው የሚታመም፣ የሚራብ፣ የሚደክም፣ የሚያለቅስ፣ የሚጠማ፣ መከራ የሚቀበልና የሚሞት ነበር። *"በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመሰል ተገባው"* ተብሎ እንደተጻፈ።- *ዕብ 2÷17*

ጌታችን ከትንሣኤው በፊት በነበሩት ጊዜያት ራሱን በክብር አልገለጠም *"ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፣ ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፣ በምሰሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ"* ፊሊ2÷ *6-8* ተብሎ የተነገረው ለዚህ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ትንሣኤ በክብር መሆኑን ሲገልጽ *"በመበሰበሰ ይዘራል ባለመበሰበሰ ይነሣል። በውርደት ይዘራል በክብር ይነሣል በድካም ይዘራል በኃይል ይነሣል፣ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል መንፈሳዊ አካል ይነሣል"* ፩ቆሮ15÷*42-44* በማለት ከትንሣኤ በፊትና በኋላ ሥጋ ያለውን ልዩነት አስረድቷል።

አሁንም ትንሣኤ በከበረ ሥጋ እንደሚፈጸም በማያሻማ አገላለጽ *"ከቡር ሥጋውን እንዲመሰል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለወጣል"* ፊሊ*3÷21* ተብሎ ተጽፏል። ጌታችን በደቀ መዛሙርቱ ፊት መብላቱ ትንሣኤውን ተጠራጥረው ስለነበር እንዲያምኑ እንጂ ከትንሣኤ በኋላ መብላት መጠጣት በመሰለ ግብር እንድናስበው አይደለም።

ዕርገቱና ዳግም ምጽአቱ እንዲሁ በከበረ ሥጋ ነው የሚሆነው። *"የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ"* ማቴ *25÷31* እና *"የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ"* ሉቃ *9÷26* የሚሉት አገላለጾች ለዚህ ማሳያ ናቸው።

Scanned by CamScanner

ጌታችን በከበረ ሥጋ የሚታወቀው ከስቅለቱ ወይም ከትንሣኤው በኋላ ስለሆነ ለደቀመዛሙርቱ "ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለ እርሱ እንደተጻፈ....ትገ አላቸው" ዮሐ 12÷16 ተብሎ ተገልጿል::

ደቀ-መዛሙርቱ እንኳ ጌታ በከበረ ሥጋ (በማይደክም በማይራብ በማይጠማ...ወዘተ) ሥጋ መነሣቱን ያወቁት ቀስ በቀስ ነው:: ለዚህ ነው መግደላዊት ማርያምን "አትከልተኛ" የመሰላት ዮሐ 20÷14-16 በተመሳሳይ ሁለቱ የኤማሁስ መንገደኞች ያን ሁሉ መንገድ አብሯቸው ሲጓዝና ሲያነጋገራቸው ያላወቁት በአንዴ ከብሩን ያልገለጸላቸው በመሆኑ ነው::- ሉቃ 24÷16

ከዚህ በመነሣት ጌታችን ከትንሣኤ በኋላ መራብ መጠማት መድከም ማዘን መታመም መሞት መሰገድ መጾም መጸለይ መከራ መቀበል መሞት የለበትም:: አሁን ያለው ሰው ከመሆኑ በፊት በነበረው ክብር ስለሆነ "አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ" ዮሐ 15÷5 በማለት ተናገረ::

ሴቶችና የጌታ ትንሣኤ

ምንም እንኳ አንዳንዶች ጌታችን ከተነሣ በኋላ መግደላዊት ማርያምን "አትንኪኝ" በማለቱ ሴት በመሆኗ አሳንሷት ነው በማለት ከርስትናን ለመተቸት ቢሞክሩም እውነታው ግን በተቃራኒው በጌታ ትንሣኤ የሴቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን የሚያስረዳ ነው::

ምክንያቱም ሴቶች ከሁሉ ቀድመው (ከሐዋርያትም ጭምር) የጌታን መነሣት ያዩና ያወቁ፣ መቃብሩ ባዶ መሆኑን የተመለከቱ፣ የጌታን ድምፅ የሰሙ አካሉን የነኩ እና ለመጀመሪያ ጊዜ የትንሣኤውን ምስራች ለደቀ-መዛሙርቱና ለሌሎች ያወሩ እነርሱ ሆነው እናገኛለንና ነው::

ይህ እንዲህ ከሆነ ታዲያ ለምን አትንኪኝ አላት የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል:: ዮሐ 20÷17 ለዚህ የሚከተለው ምክንያት ይቀርባል::

Scanned by CamScanner

ሊቀ ካህናቱ የጌታ ሥጋ ከመቃብር ተወስዷል ብለው ያስወሩት ከፉ ወሬ ተጽእኖው ለመግደላዊት ማርያምና ለደቀ-መዛሙርቱ የተረፈ ነበር። ይህ ወሬ ጌታ ከሞት መነሣቱን ለመቀበል እንዲቸገሩ አድርጓቸው ነበር። ስለዚህ መግደላዊት ማርያም ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ሦስት ጊዜ እንደካደው እርሷም የጌታን ትንሣኤ ሦስት ጊዜ ተጠራጥራለች *(ከዳለች)*።

የመጀመሪያው ጥርጣሬ፡- ለቅዱስ ጴጥሮስና ለቅዱስ ዮሐንስ የተናገረችው ነው። ንግግሩም *"እየሮጠች ወደ ሰምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር መጥታ ጌታን ከመቃብር ወሰደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም አለችው"* ዮሐ 20÷2 የሚል ነው።

ይህ አነጋገሯ ጌታ ገና እንዳልተነሣ ታምን እንደበር ከማስገንዘቡ ሌላ የጌታን ሥጋ ማንም ወስዶ ወደፈለገው ቦታ ሊያስቀምጠው እንደሚችል ታስብ እንደበር ያሳያል-ጥርጣሬ አንድ።

ሁለተኛው ጥርጣሬ፡- ይህ ደግሞ ለሁለቱ መላእክት የተናገረችው ነው *"ጌታዬን ወሰደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም አለቻቸው"* ዮሐ 20÷13 ምን ያህል ሊቀ ካህናቱ ባወሩት ወሬ ተወስዳና ለጥርጥር ተዳርጋ እንደነበር አነጋገሯ ያሳያል።

ሦስተኛው ጥርጣሬ፡- ለራሱ ለጌታ የተናገረችው ነው፡ *"አንተ ወሰደሽው እንደሆንህ ወዴት እንዳኖርሽው ንገረኝ አፄም አወስደዋለሁ አለችው"*።- ዮሐ 20÷15

ከነዚህ ሁሉ ጥርጣሬዎቿ የተነሣ ማርያም መግደላዊት *"አትንኪኝ"* ተባለች። ይህም ለተግሣጽ የተናገራት አነጋገር መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም የተጠራጠረችው የጌታን ድምፅ ከሰማችና መልኩን ከተመለከተች በኋላ ነውና።

ነገር ግን በተመለከተችና ባወቀችው ጊዜ ግን *"ረቡኒ"* ብላ ጠራችው። ረቡኒ የሚለው ቃል ከፍተኛ የሆነ ክብርንና ፍቅርን የሚያመለክት ቃል ነው። *"ረቢ"* ከሚለው ቃል የበለጠ ክብርን ያሳያል። በተጨማሪም *"ረቡኒ"* በመቃብሩ ስፍራ ለመጨረሻ ጊዜ

Scanned by CamScanner

የተጠራበት መጠሪያ ነው::ረቡኒ የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ጌታ ወይም መምህር ማለት ነው::

ስለዚህ *"አትንኪኝ"* ያላት ሴት በመሆኗ ነው የሚለው የተሳሳተ አመለካከት ውድቅ ይሆናል ማለት ነው:: አለበለዚያ ምክንያቱ ከላይ የተጠቀሰው *(ጥርጥሯ)* ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? ነገር ግን እንዲህ እንዳይባል (በሴትነቷ ነው እንዳይባል) እርሷ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁን የሰማች ብቻ ሳይሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የነካችውም እርሷ በመሆኗ ነው *"እነርሱም (ማርያም መግደላዊትና ሌላይቱ ማርያም) ቀርበው **እግሩን** ይዘው ሰገዱለት" ማቴ 28÷9* ተብሎ መንካታቸው ተረጋግጧልና::

በሌላ አተረጓጎም አባ ጊዮርጊስ ጌታ ማርያምን አትንኪኝ ማለቱ ምእመናን ሥጋውና ደሙን መንካት እንደማይገባቸው ሲያመለክት ሲሆን ሐዋርያትን *"ዳሱኝ"* ማለቱ ካህናት ሥጋውና ደሙን የመንካት ሥልጣን እንዳላቸው ያስገነዝባል ብሎ ተርጓሞታል *(መጽሐፈ ምሥጢር)*::

ወደ አባቴ አላረግሁም

ቅዱስ አውግስጢንና ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ *(Saint Severus)* ወደ አባቴ አላረግሁም የሚለውን ቃል ሲተረጉሙ ገና ሥጋዬ ምውት እንደሆነና ሰዎች እንደፈለጉ ከቦታ ወደ ቦታ እንደሚወስዱት ማሰቧን አለመተዋን እና በመለኮታዊ ከብሬ ከአባቴ ጋር አንድ መሆኔን አላመንሽም ሲላት ነው በማለት ተርጉመውታል::

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ይህን ቃል ሲተረጉም *"ገና አላረግሁም ማለቱ መለኮት በባሕርይው ምሉዕ በኩሄ ስለሆነ በሥጋ ማርያም አንዳረገ እንድንረዳ መሆኑን ገልጿል::"*

ሌሎች ሴቶች

በጌታ ትንሣኤ ከመግደላዊት ማርያምና መጽሐፍ ቅዱስ ሌላይቱ ማርያም አያለ ከሚያነሣት ማርያም ውጪ ሌሎች ሴቶችን እናገኛለን:: ስለ እነዚህ *"ሌሎች ሴቶች"* ስለተባሉት ሐኪሙ ሉቃስ ሲገልጽ *" ከገሊላም ከእርሱ ጋር (የእርማትያሱ ዮሴፍ ነው)*

Scanned by CamScanner

የመጡ ሴቶች ተከትለው መቃብሩን እንዴት እንዳኖሩት አዩ:: ተመልሰውም ሽቱና ቅባት አዘጋጁ" ሉቃ 23÷55-56 በማለት ገልጿቸዋል::

ምንአልባት እነዚህ ባላሽቱና ባለቅባት ሴቶች ጌታ ይነሣል ብለው ተስፋ ያደረጉ አይመስልም:: ምክንያቱም ከጣፋጭ ቅመም ያዘጋጁት ሽቱና ቅባት ጠቀሜታው የጌታን *ሥጋ (ቢድን)* ሳይደርቅ ለዓመታት መቆየት እንዲያስችለው ነው:: ስለዚህ ይነሣል ብለው አልጠበቁም ማለት ነው:: ነገር ግን ለጌታ ከነበራቸው ከፍተኛ ፍቅር የተነሣ ብቻ ሽቱና ቅባት አዘጋጁ ለቢድኑ ከብርን ለመግለጥ::

ይሁን እንጂ ጌታ ለአርሱ ያላቸውን ከብርና ፍቅር ይረሳ ዘንድ አመፀኛ አይደለምና (ዕብ 6÷10) ከሐዋርያት እንኳ ቀድመው ትንሣኤውን እንዲመለከቱ የምስራቹንም እንዲናገሩ በማድረግ ዋጋን ከፈላቸው:: ስለዚህ ሁኔታ ሉቃስ ሲናገር *"ይህንን (መነሣቱን) ለሐዋርያት የነገሯቸው መግደላዊት ማርያምና፣ ዮሐና፣ የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩ ሌሎች ሴቶች ነበሩ" ሉቃ 24÷10* ብሏል:: በተጨማሪም በትውፊት እንደሚነገረው እነዚህ ሴቶች የጌታ *ሥጋ* በአግባቡ መቀበሩን አረጋግጠዋል እንዲሁም እመቤታችንን በኅዘኗ ወቅት ከጐኗ በመሆን ተራድተዋታል::

የሰው ልጆች ትንሣኤ

ሞትም ሆነ ትንሣኤ በኋላ የመጡ ነገሮች እንጂ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሕይወት ያዘጋጃቸው ዓላማዎች አልነበሩም:: የመጀመሪያው ሰው አዳም ሞትን በገዛ ፈቃዱ ጠርቶ ወደ ዓለም እንዲገባ አድርጓል:: ከዚህ የተነሣ የአዳም ልጆች ሁሉ ከሞት መዳፍ የማያመልጡ ሆኑ:: ማንም ከሞት የማያመልጥ ሆነ:: ሞት በሰው በኩል እንደመጣ ትንሣኤ ሙታንም በሰው *(በክርስቶስ)* በኩል ሆኗል *(1ቆሮ 15÷20-23)* አስቀድሞ ከጌታ ሰው መሆን በፊት ከሞት የተነሡ ሰዎች ቢኖሩም ተመልሰው ሞተዋል:: አሁን ግን ክርስቶስ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ዳግመኛ ላይሞት በመነሣቱም እኛም ዳግም ሞትን የማይናይበት ትንሣኤ ስላጐናጸፈን *"የትንሣኤያችን በኩር...ተባለ"::*

Scanned by CamScanner

ስለዚህ ከጌታ ትንሣኤ በኋላ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ እርሱ እንደተነሣ እንደሚነሡ በማመንና ተስፋ በማድረግ ይኖራሉ። ስለሆነም የሙታን መነሣት በክርስትና ውስጥ አስፈላጊና ወሳኝ የሆነ ዶግማ ነው። ሌሎች ፍጥረታትና ሰውን እምሳበ አልቦ ያመጣ አምላክ ሰውን ሞቶ ፈርሶና በስብሶ ከነበረበት ማንሣት አይሳነውም። ነገር ግን አንዳንዶች ከጥንት እስከ ዛሬ ትንሣኤ ሙታን የለም በማለት ይከዳሉ። እነዚህም ተከታዮቹ ናቸው።

ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ

1. ፕሮቅያኖች *(The porchians)* እነዚህ ከ.ክ.ል በፊት በ350 የተወለደው ዚኖን zinon የተባለው ግሪካዊ ፈላስፋ ተከታዮች ናቸው። ነፍስ ሥጋን ከተወች በኋላ ነፍስ ወደ ታላቁ አምላክ *(god)* ተመልሳ ትጠፋለች ብለው ያምናሉ። በመሆነም በሙታን መነሣት አያምኑም።
2. ኤፊቆሮስዎች *(The Epicurean)* እነዚህ ከ.ክ.ል በፊት በ341 የተወለደው የኤፊቆሮስ ተከታዮች የነበሩ ናቸው። አማልክት *(gods)* ከሰዎችና ከፍላጐታቸው ኋላ አይመለከቱም ስለሆነም የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት በነፍስና ሥጋ ሞት ይደመደማል ብለው ያምኑ ነበር።

በመሆኑም ደስተኛ አኗኗርን ይመራሉ። በተጨማሪም "ንብላዕ ወንስተይ ጌሠመ ንመውት" የሚል የታወቀ ርዕዮተ ዓለም (Ideology) ነበራቸው። ትርጉሙ እንብላ እንጠጣ ነገ እንሞታለን ማለት ነው። ኤፊቆሮስዎች ቅዱስ ጳውሎስ በአቴና ሲሰብክ በመንገድ የተገናኙት ናቸው። -*የሐ 17÷18*

3. ሰምዖናውያን *(The Simoneans)*:- እነዚህ የሙታን ትንሣኤን አስፈላጊ እንዳልሆነ ያምናሉ ምክንያቱም ነፍስ በዳግም መገለጥ *(reincarnate)* በሌላ ህላዌ ትመጣለች እንዲሁም የከፉ ሰዎች ነፍስ ወደ ደካማ አካል ወይም እንስሳ አካል ይሸጋገራል ብለው የሚያምኑ ነበሩ።

Scanned by CamScanner

4. ኤሴንያውያን *(The Aseneans)*:- እነዚህ የተባሕትዎ ሕይወትን ይመሩ የነበሩና ወደ መቅደስ ከመሄድ የተከለከሉ (እምቢ ያሉ) የአይሁድ ቡድን *(ሃራጥቃ sect)* ናቸው:: እንዲሁም ገንዘብን የሚነቅፉና በዓለም መኖርን የካዱ *(ቦናቋ)* ናቸው:: በተጨማሪ አንዳንድ የግሪክ ፈላስፎችን የሚከተሉና በትንሣኤ የማያምኑ ሲሆኑ ነፍስ ከሞት በኋላ ለዘላለም ደስታን ትቀዳጃለች ብለው የሚያምኑ ናቸው::

5. ሰዱቃውያን *(The Sadducees)*:- እነዚህ በአይሁድ ዘንድ ከፍተኛ ተጽእኖ የነበራቸው ትልቅ ቡድን *(ሀራጥቃ)* ናቸው:: ዘላለማዊ ሕይወት እንደሌለና ነፍስ ከሥጋ ጋር እንደምትሞት የሚያምኑ ናቸው:: ስለዚህ በፍርድ፣ በጽድቅ ዋጋ እና በሲኦል አያምኑም:: ጌታን በትንሣኤ እና ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት ፈትነውታል::- *ማቴ 22÷ 23-32*

6. ግኖስቲኮች *(The Gnostics)*:- ግኖስቲኮች ያምኑባቸው ከነበሩ ነገሮች መካከል ቁስ አካል የጨለማ ምንጭ እንደሆነና ጋብቻ እንደ መቆሸሽና መተዳደፍ እንደሆነ ያምኑ ነበር:: ስለዚህ ጌታ ሥጋን የለበሰ መሰለ እንጂ እውነተኛ ሥጋን አልለበሰም ይላሉ:: በመሆኑም በነፍስ ትንሣኤ እንጂ በሥጋ ትንሣኤ አያምኑም:: ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ተቀላቅላ ከእርሱ ጋር ዘላለማዊ አንድነትን ትፈጥራለች ይላሉ::

   የግኖስቲኮች ስሑት የሆነ እምነት በቅዱስ ጳውሎስ ዘመን የነበረ ስለሆነ በመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክቱ ስለ ትንሣኤ *(፩ቆሮ 15)* ምላሽም ሰጣቸው::- *2ጢሞ 4÷1-5*

በዘመናችንም ከርስቲያን ተብለው እየተጠሩ በትንሣኤ የማያምኑ ክፍሎች አሉ:: ራሳቸውን" **የክርስቶስ ደቀ-መዛሙርት**" *(Disciples of Christ)* ብለው የሚጠሩ ክፍሎች ክርስቶስ በሥጋ እንዳልተነሣና በመንፈስ እንደተነሣ የሚያምኑ ሲሆኑ የሰው ትንሣኤም ተመሳሳይ ነው ይላሉ:: **ክርስቲያን ሳይንቲስቶች** የሚባሉት ደግሞ በሥጋ ትንሣኤ የማያምኑና ሞትን እንደ ሰው አላዋቂነትና እንደ አእምሮ ቅዠች የሚመለከቱ

Scanned by CamScanner

ናቸው:: **ኳከሮች** Quakers ደግሞ በሥጋ ትንሣኤ የማያምኑና ከአባሎቻቸው አብዛኛው በክርስቶስ ትንሣኤ የማያምኑ ናቸው:: ሞርሞን የተባሉት የእምነት ክፍሎች ደግሞ በሥጋ ትንሣኤ የማያምኑ ሲሆኑ እያንዳንዱ ሰው ከሦስቱ ሰማያት በአንደኛው ይኖራል የሚሉ ናቸው:: በዝርዝር ሲያስቀምጡት ቴሌስቲያል *(telestial ለማያምኑ)* ቴሬስትርያአል (terrestrial ለክርስቲያኖች ነገር ግን በሞርሞን መልእክት ያላመኑ) እና ሴሌስቲያል *(celestial ለምርጮኖች)* የሚሉ ሲሆኑ በተጨማሪም እያንዳንዱ ከቤተሰቡ ጋር በተለየ ዓለም እያስተዳደረ ይኖራል ይላሉ::

የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ ከርስቶስ እንደሰው ሞቶ እንደ ኃያል ፍጥረታዊ መንፈስ ተነሣ ይላሉ:: ሲነሣ ሥጋውን አልለበሰም ይላሉ:: በተጨማሪም ሰው ነፍስ የለውም ብለው የሚያምኑ ስለሆነ ትንሣኤ የለም ይላሉ:: **የአዲሱ ዘመን ተከታዮች** *(New age followers)* ደግሞ በዘላለማዊ ሕይወት የሚያምኑ ሲሆኑ የሟቹ ነፍስ ከአግዚአብሔር ጋር ይቀላቀላል የሚሉ ገነትና ሲኦል በዚህ ዓለም ያሉ የመጥፎና መልካም ሕሊና ደረጃዎች ናቸው ይላሉ:: እንዲሁም **ዩኒቴሪያንስ** (Unitarians) ቃል በቃል በቁሙ ትንሣኤ የለም የሚሉ ሲሆኑ እያንዳንዱ ከአንድ ቅርጽ ወደ ሌላ ሄዶ ሊገለጽ ይችላል ይላሉ::[58]

ትንሣኤ ልቡና እና ትንሣኤ ዘጉባኤ

ትንሣኤ ልቡና

ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የሰው ልጅ ሁለት ትንሣኤዎች እንዳሉት ታምናለች:: ትንሣኤ ልቡና እና ትንሣኤ ዘጉባኤ የተባሉ:: ትንሣኤ ልቡና በመጨረሻው ቀን ከመነሣታችን በፊት በንስሐና በጽድቅ አሁን የምንነሣው ትንሣኤ ነው:: ለዚህ ትንሣኤ *(ትንሣኤ ልቡና)* ጥምቀት ቁርባንና ንስሐ ወሳኝ ነገሮች ናቸው::

58. St John Magazines October 2007.

Scanned by CamScanner

ምክንያቱም ጌታ ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ በመጨረሻው ቀን ይነሣል በማለት ተናግሯልና ነው ዮሐ 6÷54 በተጨማሪም ጥምቀት ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር መካፈል እንደሆነ ተገልጿል።- ሮሜ 6÷3፣ ፩ቆሮ15÷29

ሌላው ትንሣኤ ልቡና ማግኛ መንገድ ከሞተ ኃጢአት በንስሐ መነሣት ነው። ለዚህ ነው የጠፋው ልጅ አባት ስለ ልጁ "ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኗል" ሉቃ 15÷24 በማለት የተናገረው።

ቅዱስ ጳውሎስም ኃጥእ በኃጢአት ያንቀላፋ (የሞተ) ስለሆነ እና በንስሐ የሚነሣ ስለሆነ "አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስ ያበራልሃል" ኤፌ 5÷14 በማለት የተናገረው።- ቆላ 2÷13

ይህን በንስሐ የምናገኘውን ትንሣኤ ወይም ትንሣኤ ልቡና መጽሐፍ **"ፊተኛው ትንሣኤ"** ብሎ ይጠራዋል። "ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው። በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው። ሁለተኛው ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም" ራእ 20÷5-6። ከጥቅሱ የምንረዳው የፊተኛው ትንሣኤ (ትንሣኤ ልቡና) ለሁለተኛው ትንሣኤ (ትንሣኤ ዘጉባኤ)ዋስትና እንደሆነ ነው። ስለዚህ ሰው በጥምቀት በቁርባንና በንስሐ ሕይወት የተነሣ ለሁለተኛው ትንሣኤ ተስፋ ይኖረዋል።

ትንሣኤ ዘጉባኤ

በመጨረሻው ዘመን በጌታችን ዳግም ምጽአት የሞቱ ሁሉ ይነሣሉ። ይህ በቤተ ክርስቲያን አጠራር ትንሣኤ ዘጉባኤ ይባላል። የማኅበር ትንሣኤ ማለት ነው። ምክንያቱም በመጨረሻው ቀን የሞቱ ሁሉ ተነሥተው ለፍርድ የሚቀርቡበትና ጻድቃን ወደ ዘላለም ክብር ኃጥአንም ወደ ዘላለም ሀሳር የሚሄዱበት ስለሆነ ነው።

በትንሣኤ ዘጉባኤ በመነሣት ጻድቃንም ኃጥአንም አንድ ናቸው። ልዩነቱ ጻድቃን **ትንሣኤ ዘለክብር** ሲነሡ ኃጥአን ግን **ትንሣኤ ዘለሀሳር** መነሣታቸው ነው። በዚህ ቀን የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች እንደሚሉት ጻድቃን ብቻ የሚነሡበት አይደለም። ለሁለቱም ለኃጥአንም ለጻድቃንም ትንሣኤ ይሆናል።- ዮሐ 24÷15

Scanned by CamScanner

ጌታችን ስለ ሁለቱ ትንሣኤ ማለት ስለ ትንሣኤ ልቡናና ትንሣኤ ዘጉባኤ ተናግሯል፡፡ *"እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል አርሱም አሁን ነው የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ (ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ወይም ትንሣኤ ልቡና ነው)... በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉን ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ (ይህ ትንሣኤ ዘጉባኤ ነው)"* -ዮሐ 5÷25-29፣ራእ 1÷7

የማይነሡ የሚነጠቁ!

መጻሕፍት የማይሞቱና የማይነሡ ወገኖች እንዳሉ በሚመስል ሁኔታ የሚናገሩበት ሁኔታ አለ፡፡ ታዲያ እነዚህ ምን ይሆናሉ ከተባለ ጌታ በሚመጣበት ቀን በሕይወት ያሉ ጻድቃን አይሞቱምም አይነሡምም፤ ዳሩ ግን በደመና ይነጠቃሉ ወይም ያርጋሉ፡፡ ስለዚህ ነገር ሐዋርያው ሲናገር *"እነሆ፣ አንድ ምሥጢር አነግራችኋለሁ ሁላችን አናንቀላፋም"* 1ቆሮ15÷51 በማለት ገልጾታል፡፡ዳግመኛም *"በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ (ሁለተኛው ትንሣኤ ነው) ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው (በጊዜው ሕያዋን የሆኑ) ጌታን በአየር ለመቀበል ከአርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን"* 1ተሰሎ 4÷15-17* በማለት ጌታ በሚመጣበት ጊዜ በሕይወት ያሉት ሕያዋን መሞት ወይም መነሣት እንደማያገኛቸው ይልቁንም ዕድል ፈንታቸው መነጠቅ እንደሆነ ተናገረ፡፡ *(የቅዱስ ጳውሎስ ትርጓሜ ገጽ 192 እና 340)*

የመለከት ድምፅ

ጌታ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ መላእክት የመለከት ድምፅ ያሰማሉ ማቴ 24÷31፣1ቆሮ 15÷52፣1ተሰ 4÷16፡፡ ሁኔታው ልክ ጌታ ወደ ደብረ ሲና ሲወርድ ከነበረው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ *"እንዲህም ሆነ በሦስተኛው ቀን በማለዳ ጊዜ*

* በሌላ በኩል ሰዎች ሁሉ የሚሞቱና የሚነሡ በመሆኑ "እንነጠቃለን" ተብሎ መገለጹ የሚያሳየው የማይሞቱ ሰዎች እንዳሉ ሳይሆን በትንሣኤ የሚኖረውን ባለሚልነት (የከብር ደረጃ) ነው የሚል አመለካከት አለ፡፡

Scanned by CamScanner

ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና አጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምፅ በተራራው ላይ ሆነ በሰፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተንቀጠቀጡ" ::-ዘዳ 19÷16

የመለከት ድምፅ ምሳሌ ሲሆን የጌታ ትእዛዝ ነው:: በጌታ ትእዛዝ ሙታን ከያሉበት የሚሰበሰቡ ስለሆነ በመለከት ድምፅ ተመስሏል *ዮሐ 5÷29* ::መለከት ሦስት ጊዜ ይነፋል፣ በመጀመሪያው ንፍሐተ ቀርን (የመለከት ድምፅ) ፈርሶና በስብሶ የነበረው የሰው ሥጋ ከያለበት ይሰበሰባል:: በሁለተኛው ንፍሐተ ቀርን የተሰበሰው ሥጋ ተያይዞ ሙሉ አካል ሆኖ ትኩስ በድን ይሆናል:: በሦስተኛው ንፍሐተ ቀርን ነፍስ ከአለችበት መጥታ ከሥጋ ጋር በመዋሐድ ሕያው ሆኖ ይነሣል::- *1ቆሮ 15÷52*

አርጌንስ (*Origen*)የማቴዎስ ወንጌልን ሲተረጉም በበኩሉ ስለ ንፍሐተ ቀርን ሲናገር፣ በመድኅን ክርስቶስ ተልከው የተመረጡትን ለመሰብሰብ የተላኩ መላእክት መጽሐፍ የ*"ታላቅ መለከት ድምፅ " ማቴ 24÷31* ብሎ በሚጠራው ድምፅ እንጂ ተርታ በሆነ ድምፅ አይሰበስቡም ብሏል::

ይህ ድምፅ ያልታወቀ ድምፅ አይደለም፤ ይልቁንም የታወቀና ግልጽ ነው እንጂ፤ ስለሆነም ለሚሰሙና ላስተዋሉት ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ልጅ የሚወስደውን ፍጹሙን መንገድ የሚመሠርት ነው ብሏል::

ጌታችን *"ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም" ማቴ 24÷35* ብሏል:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን በተመለከተ ሲናገር ጌታ መናገር የፈለገው ሰማይና ምድር እኛን ለማገልገል *(ለእኛ ጥቅም)* እንደተፈጠሩ መግለጥ ነው፤ ነገር ግን የእርሱ ቃል የተነገረው እኛን ለመግዛት *(ለማስተዳደር)* ነው ሲል ተርጉሞታል፤ ቅዱስ ጳውሎስም *"ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቷልና " ሮሜ 8÷20* በማለት እንደተናገረው ነው ሲል ገልጾታል::

Scanned by CamScanner

በምን ዓይነት ሁኔታ እንነሣለን?

ቅዱስ ጳውሎስ ስለሁኔታው ሲገልጽ *"ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፣ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም "* *1ቆሮ 15÷50* በማለት አስተምሮአል። በዚህ መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ጻሕፍት (*የሐዲሰ ኪዳን*) ስለ ትንሣኤ ሲናገሩ ስለ *ሥጋ (flesh, sarkis በግሪክ)* አልተናገሩም ይልቁንም ስለ አካል *(body በግሪክኛ soma)* ተናገሩ እንጂ። ቅዱስ ጳውሎስ *" ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፣ መንፈሳዊ አካል ይነሣል "* *1ቆሮ 15÷42* በማለት የተናገረው ለዚህ ነው። ፍጥረታዊ አካል ሟችና በስባሽ ስለሆነ *(ሮሜ 6÷12፣8÷11)* የግድ የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን መልበስ አለበት።- *1ቆሮ 15÷53*

አበው ሊቃውንት ከትንሣኤ በኋላ የሚኖረን አካል ከመሞታችን በፊት ከነበረን አካል ጋር አንድ እንደሆነ ተናግረዋል። ልዩነቱ የማይሞትና የማይበሰብስ ወደመሆን መለወጡ ብቻ ነው። ይህ መለወጥ የማይሆን ከሆነ ትንሣኤ ረብ የሌለው ይሆናል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሞተው አካልና የሚነሣው አካል ተመሳሳይ ዘር (genesis) ያላቸው መሆኑን ተናግሯል። *" ይህን ቤተ መቅደስ (ሰውነቱን) አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ "* *ዮሐ 2÷19* የሚለው ቃል የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ሁለቱም የሞተውም ሆነ የተነሣው አካል ተመሳሳይ ዘር (genesis) እንዳላቸው ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሐሳብ በዘር ምሳሌ ግልጽ አድርጐታል። ይኸውም የሚበቅለው ከተዘራው የመጣ ነው ብሏል። ሁለቱም *(ዘርና ተክል)* ተመሳሳይ ዝርያ ናቸው፣ ነገር ግን ተክል *(የበቀለው)* የበለጠ አስፈላጊ ነው። የተነሣው የቅዱሳን አካልም እንዲሁ በተመሳሳይ የከበረ አካል ይሆናል። ጌታችን እነዚህን ዘላለማዊ ሕይወትን መቀበልና ተስማሚ መሆን እንዲችሉ ወደ መንፈሳዊ አካል ይለውጣቸዋል። *" ጌታን ኢየሱስ ከርስቶስን እንጠባበቃለን እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ የሚችልበት አሠራር፣ ከቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል"* *ፊሊ 3÷21* እንዲል።- *1ቆሮ 15÷51-52*

Scanned by CamScanner

ከሞት መነሣት ወይም ትንሣኤ ለኃጥአንም ለጻድቃንም የሚፈጸም እንደሆነ ተመልከተናል:: ነገር ግን ሁለቱንም ከትንሣኤ በኋላ አንድ የሚያደርጓቸው ባሕርያት እንዳሉ ሁሉ ልዩ የሚያደርጋቸው ባሕርያት አሉ::

ኃጥአንም ሆኑ ጻድቃን ከሚጋርዋቸው ባሕርያት ውስጥ ኢመዋቲነት፣ ማንነት *(ተለይቶ መታወቅ)* እና የተሟላ ሰብአዊ ቅርጽ ተጠቃሾች ናቸው::

ጻድቃንን ለብቻ ልዩ የሚያደርጋቸው ባሕርያት:-

1. ከቡርነት እና ብርሃናዊነት::- ማቴ 13÷43፣ 1ቆሮ 15÷43፣ ፊሊ3÷21 ራእ 19÷8
2. እንደ ተነሣው ከርስቶስ ዝግ የሆኑ ነገሮችን ዘልቆ መግባት መቻል ዮሐ 20÷19-20፣26÷27፣ ሉቃ 24÷36-40፣1ዮሐ.መ 3÷2 "እርሱን እንድንመስል እናውቃለን" እንደ ተባለ::
3. ፍጥነትና ኃያልነት በፍጥነት እንደ መላእክት መንቀሳቀስ መቻል::- 1ቆሮ 15÷43
4. ስለ ብዙ ነገር አዋቂ መሆን ሉቃ 16÷25 እና 29 ::-1ቆሮ 13÷12
5. በአዲስ ምድርና በአዲስ ሰማይ በአዲሲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም መኖር እና ሁሉን ነገር መውረስ ሮሜ 8÷17፣ 2ጴጥ 3÷13::- ራእ21÷1-7
6. ጽድቅን በተሞላ ስፍራ እግዚአብሔርን በማከበር በሰማያዊ መንግሥቱ መኖር::- ማቴ 8÷11፣ ማቴ 25÷34፣ ሉቃ 12÷32፣ 2ጴጥ3÷13 2ጢሞ 4÷1
7. ከመላእክት ጋር ማመስገንና ማወደስ::- ራእ 7÷9-12፣ ራእ19÷1-7
8. ከነቢያት ከቅዱሳን ከሰማዕታት በሁሉም አገር ነገድ ቋንቋ ከነበሩ ቅዱሳን ሰዎች እና ሰማያውያን ሠራዊት ጋር ሆኖ በአንድነት መደሰት እና እነርሱን ማየት::-ሉቃ 13÷28-29፣ ይሁዳ14፣ ራእ7÷9-17፣19÷1
9. ያለ ሕማም ችግርና ሰቃይ መኖር::- ኢሳ 33÷24ራእ 21÷4
10. እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ማየትና ለዘላለም ከእርሱ ጋር መኖር::-1ዮሐ 3÷2፣ራእ 21÷3፣ራእ 22÷4

Scanned by CamScanner